
# የፍቅር ምስል



ትምህርት 7 ለ ነሐሴ 9፣ 2018

“እንዲህም ከሆነ፥ እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።”

(1 ቆሮንቶስ 13:13)



1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 “የፍቅር ምዕራፍ” በመባል ይታወቃል። የሚያትተውም ስለ ባልና ሚስት ፍቅር ሳይሆን ከዚህም ይልቅ የጠለቀውን የመለኮት ፍቅርን ነው።

ጳውሎስ በልባችን የፈሰሰውን የእግዚአብሔርን ፍቅር በሚያስደንቅ መልኩ በሕይወታችን እንዴት መግለጥ እንደምንችል አብራርቶልናል (ሮሜ 5:5)።

ፍቅር የድርጊቶቻችን ሁሉ አንቀሳቃሽ መንስኤና አብረውን ላሉት ጥቅም እንድንሰራ የሚያነሳሳን ምክንያት ነው።





## የፍቅር ምስል

- የፍቅር የበላይነት
  - ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ
- የፍቅር ባህሪ
  - የፍቅር ተግባር የሆነው
  - የፍቅር ተግባር ያልሆነው
  - የኢየሱስ ምስል
- የፍቅር ጽናት
  - ከሁሉ የሚበልጠው ጸጋ

# የፍቅር የበላይነት

Ágape

# ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ

"ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ። ደግሞም ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ አሳያችኋለሁ።" (1 ቆሮንቶስ 12:31)




ጳውሎስ በ 1ኛ ቆሮንቶስ 13 ያቀረበው ፍቅር ምን አይነት ነው እናም ማንኛውንም መንፈሳዊ ስጦታ የሚበልጠው ለምንድን ነው? (1ቆሮ 12:31-13:3)

በግሪክ ቋንቋ ውስጥ ፍቅርን የሚገልጹ በርካታ ቃላት አሉ። ጳውሎስ አጋፔ የሚለውን ቃል መርጧል፤ ይህም ፍቅር የተወዳጁን ደህንነት ብቻ የሚፈልግ፣ ከእኔነት የነፃ እና በሁኔታ ያልተቃኘ ፍቅር ነው። ዮሐንስ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" ለማለት የተጠቀመው ቃልም ይኸው ነው (1 ዮሐ 4:8)።



ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ በእንደዚህ አይነት ፍቅር ካልታጀበ በቀር አይጠቅምም። እንዳውም ድርጊታችንና ሀሳባችን በሙሉ በአጋፔ ፍቅር የተሞላ መሆን አለበት።



ኢየሱስ በክፋት ምክንያት ይህ ፍቅር ወደ ፊት እንደሚቀዘቅዝ አስጠንቅቆ ነበር (ማቴ 24:12)። ነገር ግን ይህ በእኛ ላይ፣ በቤታችን ወይም በቤተክርስቲያናችን ውስጥ እንዲሆን መፍቀድ የለብንም።

# የፍቅር ባህሪ

# የፍቅር ተግባር የሆነው

"ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል [...] ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።" (1 ቆሮንቶስ 13:4-7)

| | | |
|---|---|---|
| ይታገሳል | *ማክሮቱሚአ*: የሚታገስ መንፈስን መያዝ፣ ቻይ መሆን፣ ታጋሽ መሆን | የሌሎችን ስህተት ይታግገሳል ይችላል |
| ቸርነት ያደርጋል | *ኽሬስቲዎማይ* : ቸር ያደርጋል | መሀሪና አዛኝ ነው |
| ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል | *ሱንግኻይሮ* : መስማማት፣ ማወደስ | እውነቱን ከሚደግፉ ጋር አብሮ ደስ ይለዋል |
| ሁሉን ይታገሳል | *ስቴጎ* : በዝምታ ማለፍ (በትዕግስት መቻል) | የሌሎችን ስህተት የሚሸፍን፣ ሚስጥራቸውን የሚጠብቅና የማያጋልጥ ነው |
| ሁሉን ያምናል | *ፒስቲውዖ* : የእምነት ሰው መሆን፣ ለሌሎች እውቅና መስጠት፣ ሌሎችን ማመን | ለጥርጣሬ በር ሳይከፍት ያምናል እንጂ አይፈርጅም |
| በሁሉም ተስፋ ያደርጋል | *ኤልፒዞ* : መጠበቅ ወይም እንደሚሆን ማመን | ሁል ጊዜ መልካሙን ይጠብቃል |
| በሁሉ ይጸናል | *ሁፖሜኖ* : መቋቋም፣ መቻል፣ መጽናት፣ በጽናት ማለፍ | አስቸጋሪ ሁኔታዎችን፣ ፈተናዎች እና ስደትን ይቋቋማል |



# የፍቅር ተግባር ያልሆነው

"[...] ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤[...] ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም"
(1 ቆሮንቶስ 13:4-7)



| | | |
|---|---|---|
| አይቀናም | ዜይሎዖ : የሚነድድ ስሜት | የሌሎችን ስጦታ ወይም ችሎታ አይመኝም |
| አይመካም | ፔርፔሪውዖማይ : ጉራ፣ መመካት | በሌሎች መሞገስ አይፈልግም |
| አይታበይም | ፉሲዖ : መኮፈስ፣ መታበይ | ራሱን ከፍ አድርጎ አያይም |
| የማይገባውን አያደርግም | አስኬሞኔዮ : ያልተገባውን ማድረግ | የማህበራዊና የስነ-ምግባር ስርዓትን አይጥስም |
| የራሱን አይፈልግም | ዜይቴዖ : መፈለግ | ለሌሎች ጥቅም የራሱን መብት ይተዋል |
| አይበሳጭም | ፓሮክሱኖ: ማነሳሳት፣ ማበሳጨት፣ መፈታተን፣ ትዕግስት ማስጨረስ | በቀላሉ የሚበሳጭ አይደለም |
| በደልን አይቆጥርም | ሎጊዞማይ : መቁጠር | የደረሰበትን በደል ይቅር ይላል ይተዋል |
| በዓመፃ ደስ አይለውም | ኻይሮ : ሐሴት ማድረግ፣ መደሰት | ክፉ ስራን ያርማል እንጂ አይደሰትበትም |

# የኢየሱስ ምስል

"እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።" (ዮሐንስ 15:12)

ሲመቱት፣ ሲሰድቡትና ሲጠሉት ታግሷል (ማቴ 27:27-31)

ኢየሱስ ይታገሳል



ለተቸገሩት ሁሉ ያዝን ነበር

ቸር ነበር



እውነቱን በግልጽና በትክክል ያስተምር ነበር

በእውነት ደስ ይለዋል



ኃጥያተኛዋን ሴት አልፈረደባትም ይቅር አላት እንጂ (ዮሐ 8:10-11)

ሁሉን ይታገሳል



የዘኬዎስን ቸርነት አምኖ ነበረ (ሉቃ 19:8-9)

ኢየሱስ ሁሉንም ያምናል



12 ሰዎችን ይሆናል ተብሎ ለማይታሰብ ተልዕኮ ሲያዘጋጅ ነበር

በሁሉም ተስፋ ያደርጋል



ረሃብን፣ ተቃውሞን፣ ሕመምን እና ስደትን ተቋቁሞ ነበር

በሁሉም ይጸናል



# የኢየሱስ ምስል

"እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።" (ዮሐንስ 15:12)

**ክብርን አልፈለገም፤ ከተዋረዱትም ጋር ሆነ**

ኢየሱስ የራሱን አልፈለገም



**የዓለማት ንጉሥ ቢሆን በዚህ አልተመካም**

አይመካም



**የተዋረዱ ስራዎችን ለመስራት ፈቃደኛ ነበር**

አይታበይም



**ሁሉንም ሰው በአክብሮት ይይዝ ነበር**

የማይገባውን አያደርግም



**ሁልጊዜ የአባቱን ፈቃድ ይፈጽም ነበር (ዮሐ 6:38)**

የራሱን አይፈልግም



**ሲመቱት እንኳን ምላሹ የአክብሮት ነበር (ዮሐ 18:22-23)**

አይበሳጭም



**ሲሰቅሉት ለነበሩ ሰዎች ይቅርታን ይለምን ነበር (ሉቃ 23:34)**

በደልን አይቆጥርም



**ግብዞቹን ፈሪሳውያንን ይገስፃቸው ነበር (ማቴ 23:27-28)**

በዓመፃ ደስ አይለውም




# የፍቅር ጽናት

# ከሁሉ የሚበልጠው ጸጋ

"እንዲህም ከሆነ፥ እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።"
(1 ቆሮንቶስ 13:13)

የፍቅር ያልሆኑ ተግባራት በቆሮንቶስ ሰዎች ባህሪ ውስጥ ይታዩ ነበር። የሚቀኑ፣ ትምክህተኞች፣ ያልተገባን ነገር የሚያደርጉ፣ ራስ ወዳዶች፣ የሚበሳጩ፣ የሚመቀኙ እና ኃጥያትን የማይጸየፉ ነበሩ።



ታዲያ እኛ ከእነዚህ ስህተቶች በመቆጠብ ጳውሎስ እንዳስተማረን የፍቅር እሴቶችን ማካበትና መንፈሳዊ ስጦታዎችን በአግባቡ መጠቀም መቻል አለብን። ጳውሎስ ከፍቅር በተጨማሪ እምነትንና ተስፋን እንድንይዝም ያስተምረናል።





ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ኃጥያት ይጠፋል እኛም ከእርሱ ጋር ወደ ዘላለም ሕይወት በደስታ እንገባለን። ከዚያም ትንቢት፣ ልሳን እና ሌሎች ስጦታዎች፣ እምነትንና ተስፋን ጨምሮ፣ ይቀራሉ። ነገር ግን ፍቅር ለዘላለም ይጸናል (1 ቆሮ 13:8)።

“እግዚአብሔር ፍቅር ነው። የአብ እና የወልድ ፍቅር ለእያንዳንዱ አማኝ የሚበረከት ነው። የእግዚአብሔር ቃል የመለኮት ፍቅር ለሰው ልጆች የሚተላለፍበት መስመር ነው። የእግዚአብሔር እውነት ወደ አስተዋይነት የሚያደርስ መንገድ ነው። ከሰማያዊ አካላት ጋር በመተባበር ለሚሰሩ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ይሰጣቸዋል። ይህም ልብንና ባህሪን ይለውጣል፤ አማኙንም የማይታየውን እያየ እንዲጸና ያስችለዋል። ፍጹም ፍቅርን ማጣጣም የሚቻለው እውነቱን በማመንና መንፈስ ቅዱስን በመቀበል ብቻ ነው።”

EGW (Our Father Cares, October 9)